የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅ እና
የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሃገረ ስብከት
ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of New York, Northeast, Southeast and
Central United States of America

ቁጥር 132/2015
ቀን 11/13/2015

በሀገረ ስብከታችን ውስጥ ላላችሁ አብያተ ክርስቲያናት፣
በያላችሁበት

## የማትደገመዋ ጥምቀት ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን የምትሰጠዋ ብቻ ናት!

በሀገረ ስብከታችን ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕገ ሃይማኖትን እና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመጣስ፣ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም አንገዛም በማለታቸው ምክንያት ሥልጣነ ክህነታቸው የተያዘባቸው ግለሰቦች መኖራቸው ለቅዱስ ሲኖዶስና በሀገረ ስብከታችን ለምትገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የታወቀ ነው። ይኸም ጉዳይ ከሃያ ወራት በላይ ያስቆጠረ መሆኑ ይታወቃል። ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስና ብፁዕ አቡነ ዳንኤል ይኸንን ጠንቅቀው እያወቁ በሀገረ ስብከታችን ጣልቃ በመግባት ከተወገዙ ካህናት ጋር አብረው በማገልገል ተጸጽተው ወደ ቀደመ ክብራቸው እንዳይመለሱ ለስህተታቸው ተጨማሪ ድጋፍ በመሆን በዚህ ደብዳቤ የመጨረሻው ክፍል ላይ በዝርዝር እንደተገለጸው እያበረታቱ ይገኛሉ። ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ አንዲት የተዋሕዶ ሃይማኖታችን ሥርዓት መጠበቅ ሲባል በውጭው ዓለም ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት በአንድ አመራር ሥር ሆነው ሥርዓተ አምልኳቸውን እንዲፈጽሙ ጥሪውን ካስተላለፈ ዓመታት አልፈውታል። ይህን ሲኖዶሳዊ ጥሪ ተከትሎም በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ተዋሕዶ ሃይማኖታዊ አመራር ለመመራት ወስነው አገልግሎታቸውን በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ይህ የታወቀ ሆኖ እያለ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስና ብፁዕ አቡነ ዳንኤል ሕጉና ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት መክረውና አስተምረው ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲገቡ በማድረግ ፋንታ በቀድሞው የሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉ የተወገዙ ካህናት «ውግዘቱ እንዲሁ ተነሥቶላቸው ባሉበት ይቀጥሉ» በማለት ከሕጉና ከሥርዓቱ የወጣ ሁኔታ እንዲፈጸም በመፈለጋቸው ቅዱስ ሲኖዶሱ እነርሱ ባሉበት ላፀደቀው መመሪያ ዕንቅፋት ሆነውበታል። ብፁዕ አቡነ ዳንኤል ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሃይማኖታዊ መመሪያ ይልቅ የግለሰብ አጀንዳን ቦታ በመስጠት በሕክምና ስም ያለ ሀገረ ስብከታችን ዕውቅና ወደ ሀገረ ስብከታችን በመምጣት ሥልጣነ ክህነት ለሌላቸው ውጉዛን ሊጠሩበት የማይገባ የማዕረግ ስም በመስጠት ተፈታትነውናል። ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስም እንዲሁ በሕክምና ስም አመካኝተው በመምጣት ከጥፋት ሥራ ጋር መተባበርን መርጠዋል።

ይህ ጣልቃ ገብነታቸውን የበለጠ አሳዛኝ የሚያደርገው ሥልጣነ ክህነት ባላቸው ካህናት ብቻ አንድ ጊዜ ልትፈጸም የሚገባትን ጥምቀት በማቃለል የተወገዙ ካህናት በድፍረት እየፈጸሙት ያሉትን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲቀጥሉበት ማደፋፈራቸው ነው። በቅዱስ ወንጌል ላይ እንደተጻፈው ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበትና በተዘጋ ደጅ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» ብሎ የገባው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው።



140-142 W 176th Street Bronx, New York 10453
Tel. 718-466-0600/718-299-2741 Fax 718-466-1271

ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» በማለት ለደቀ መዛሙርቱ በመስጠት የጀመራት ሥልጣነ ክህነት በሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ለእኛ ትውልድም ደርሳ በሐዋርያት እግር የተተካን እኛ ሊቃነ ጳጳሳትም እንደተሠራልን ሥርዓት በመንፈስ ለምንወልዳቸው ልጆቻችን ይህችን ሥልጣነ ክህነት በመድኃኒታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንሰጣለን።

ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቁረብ፣ ናዝዞ ማሰናበት፣ መንፈስ ቅዱስን ማሳደርና ከሥላሴ ልጅነትን ማሰጠት የሚችለው ይህች ሥልጣነ ክህነት ያለችው ካህን ብቻ ነው። «ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም» የተባለለት መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እንኳን «እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል» እንዳለ ይህች የዮሐንስ ጥምቀት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያጠምቃት ጥምቀት መደገም ነበረባት።

በአንጻሩ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ እንደተጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ ከአቴና ወደ ቆሮንቶስ ሄዶ «ኢዮስጦስ ወደሚባል እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት ገባ ቤቱም በምኩራብ አጠገብ ነበረ። የምኵራብ አለቃ ቀርስጶስም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ፥ ከቆሮንቶስ ሰዎችም ብዙ በሰሙ ጊዜ አምነው ተጠመቁ» የተባለላት ያቺ ጥምቀት ግን መንፈስ ቅዱስን ማሳደርና ከሥላሴ ልጅነትን ማሰጠት በሚችል ሐዋርያ ተፈጽማለችና ፈጽሞ አትደገምም።

ከሥላሴ ልጅነት ማሰጠትና መንፈስ ቅዱስንም ማሳደር የሚቻለው ሥልጣነ ክህነት ያለው ካህን በሥርዓት በሚፈጽመው ጸሎት አማካኝነት በዕለተ ዓርብ ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከቀኝ ጎኑ በፈሰሰው ማየ ገቦ በምትፈጸም ጥምቀት ብቻ እንጂ ማንም የተወገዘና ሥልጣነ ክህነቱ የተገፈፈ ሸንቃጣ ደብተራ እንደ ቱቻ በውኃ ነክሮ ስላወጣ ብቻ ፈጽሞ የሥላሴ ልጅነት አትሰጥም! ይህንንም በድፍረት እንፈጽማለን ባሉ ላይ ሐዋርያት ውግዘትን ሲያስተላልፉ ኖረዋል። ሃይማኖታችን የድንበር ምልክቷ ሳይጠፋ ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድም በዘመናችን ይህ ሲፈጸም አይቶ እንዳላዩ ማለፍ ማናችንንም ቢሆን ከመጠየቅ አያድነንም - እየተቀለደ ያለው በሥላሴ ልጅነት ላይ ነውና። ነቢዩ ዮናስን «አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፥ በአንድ ሌሊት ለበቀለች፥ በአንድ ሌሊትም ለደረቀችው ቅል አዝነሃል። እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን የማይለዩ፣ «አበ» «እመ» ማለትን ለማይችሉ ከመቶ ሀያ ሺህ የሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሶች ላሉባት ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን?» እንዳለ በአንድ ሌሊት በቅሎ በአንድ ሌሊት የደረቀና ከጥፋቱ ተጸጽቶ ክህነቱን እንዲያስመልስ መንገዱን ሁሉ ክፍት ያደረግንለት ደብተራ በአመለካከት የሚደግፉትንና የሚያዝኑለትን ሊቃነ ጳጳሳትን በየጊዜው እያስመጣ በተገፈፈ ክህነት ከሥላሴ ልጅነት አሰጣለሁ እያለ በትዕቢትና በማን አለብኝነት ግራና ቀኛቸውን ለማይለዩ ሕፃናት በአርባ እና በሰማንያ ቀን በምትሰጥ የሥላሴ ልጅነት ላይ ሲቀልድና ግፍን ሲሠራ ማየት ለእኔ የቅዱስ ሲኖዶስን ኃላፊነት ተሸክሜ ላለሁ ለሊቀ ጳጳሱ እንደምን አያሳዝነኝ? የበለጠም የሚያሳዝነኝ የተቀበልናት ኃላፊነት እኩል ሆና እያለ፣ ልናስፈጽማት የገባናት ቃል ኪዳን አንዲት ሆና እያለ፣ የተሰጠችንም ትዕዛዝም ፍጽምት ሆና እያለ አንድን የተወገዘ ካህን በጥፋቱ እንዲቀጥል፣ በተገፈፈ ሥልጣን እንዲያጠምቅና የሥላሴ ልጅነት አሰጣለሁ ብሎ በሕፃናቱ ላይ እንዲቀልድ በቦታው ሆነው በተናገሩትና ዓለም ሁሉ እንዲያየው ሰዎቹ ባሰራጩት ቪዲዮ ላይ ብፁዕ አቡነ ዳንኤልና ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ማደፋፈራቸው ነው።

አቡነ ዳንኤል በመልእክታቸው ማብቂያ ከፈገግታ ጋር ለተወገዘው ካህን «***ዋናውን ቁም ነገር ተናግሬልሃለሁ አይደል ? ደስ ይበልህ እንግዲህ***» በማለት ግልጽ እንዳደረጉት ከኢትዮጵያ ድረስ የተመጣለት ዋናው ዓላማ እርሱን ደስ አሰኝቶ ግራና ቀኛቸውን በማይለዩና «አበ» «እመ» ማለትን በማይችሉ ሕፃናት ላይ ፈርዶ ለመሄድ መሆኑ በገሐድ የታየ ነው። በልጆቻቸው ላይ የተፈጸመው ይህ በደል የተሰማቸው በርካታ  ወላጆች እኔ ሊቀ ጳጳሱ ድረስ በመምጣት ምክርና ፈቃድን በመጠየቅ በሕጋውያን ካህናትና በሥርዓት በምትመራ ቤተ ክርስቲያን የማትነጠቅ የሥላሴ ልጅነትን አሰጥተው ነበርና።

የተወገዘ ካህን ማጥመቅና መንፈስ ቅዱስንም ማሰጠት እንደማይችል በግልጽ የታወቀ የክርስትና ሀ-ሁ ሆኖ እያለና፣ አንድ ሊቀ ጳጳስ በሌላ ሊቀ ጳጳስ ሃገረ ስብከት ጣልቃ መግባት ፍጽሞ የተከለከለ መሆኑ በሕግ ተደንግጎ እያለ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የተወገዘ ካህን ያጠመቀውን ጥምቀት እንደ ጥምቀት ቆጥረውለት **«ይህች ጥምቀትህ ሕጋዊ ናትና መደገም የለባትም ይህችን ጥምቀት መድገም ሻወር እንደመውሰድ ነው»** ማለታቸው የሥላሴ ልጅነትን በምታሰጥ በአንዲት ጥምቀት ላይ መቀለድ ነው። ቤተ ክርስቲያንን በዓለማዊ ፍርድ ቤት በመክሰስና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተደረገ ድምጽ መስጫ ካርድ ላይ «ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ መዋቅር ነፃ መሆንን እደግፋለሁ» ብለው በገዛ ፈቃዳቸው የተለዩትን **«በቤተ ክርስቲያን ጉያ ውስጥ ናችሁ - ባትሆኑማ ኖሮ እኔም ባልመጣሁ ነበር»** ማለታቸው ቤተ ክርስቲያን ስንት ጉያ አላት? ብለን እንድንጠይቅ አስገድዶናል፤ እነዚህ ሰዎች የምናውቀውና ያለንበትን አንዱን ጉያዋን ንቀው ስለወጡ በዚህ የሉምና። ብፁዕ አቡነ ዳንኤልም በስደት ያለውን ወገናችንን ወደ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጉያ መሰብሰብ የሊቀ ጳጳስነት ግዴታቸው ሆኖ እያለ በአደባባይ ከቅዱስ ሲኖዶስ ተገልለን መኖርን እንመርጣለን ያሉትን **«ከዚህ የትም እንዳትሄዱ - እዚህ ባላችሁበት ሆናችሁ ቤተ ክርስቲያን ታውቃችኋለች፣ ቅዱስ ሲኖዶስም ያውቃችኋል»** በማለት አደራ የሰጣቸውን፣ መመሪያውንም አብረው ያስተላለፉትንና አባል የሆኑበትን ቅዱስ ሲኖዶስ መናቅና ማቃለልን እንዲሁም ከራሳቸው ጋር ደግመው ደጋግመው መጋጨትን መርጠዋል። ይባስ ብለውም የተወገዘ ካህን ያጠመቀውን ጥምቀት አይሰራምና ይደገም መባሉን አስመልክተው «ቅዱስ ሲኖዶስ ይኼን መስማት የለበትም - ይህን ከሰማ ፍጹም እርምጃ ይወስዳል - ያስሽራል - እርቃነ ሥጋን ይሰዳል» በማለት ለመድረክ የጭብጨባ ፍጆታ የሚሆን ባዶ ንግግርን አድርገዋል። እኛስ የምንሰራው የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ቀኖና እያገናዘብን፣ ቅዱስ ሲኖዶስን እያማከርንና እያሳወቅን ነውና ይህንን ደብዳቤና በዚያ መድረክ በሰው ፊት ሞገስን ለማግኘት የተነገረውን ሁሉ ቅጅ በመላክ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲያውቀው አድርገናል።

በቀረውስ በዚያ የቀራችሁ ምዕመናን፡- ከቅዱስ ሲኖዶስና ከተደነገገው ሥርዓቱ ይልቅ ሁለቱን አባቶች ተማጽኖና አሳምኖ የማትጠቅም ምስክርነትን ያገኘ የተወገዘ ደብተራ እሰጣታለሁ የሚላትንና ዋጋ የሌላት ጥምቀትን እውነተኛ ናት ብላችሁ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፤ የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ፥ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና፤ ዛሬ ድምጹን ብትሰሙት፥ በማስመረር እንደሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» እንዳለ በእልኸኛነት ተመርታችሁ ቀኝና ግራቸውን በማይለዩ ሕፃናት ላይ በመፍረድ ማስጠመቁን ትታችሁ ብዙዎች ወንድሞችና እህቶቻችሁ እያደረጉ እንዳሉት ሁሉ ቀሪዎቻችሁም ወደ ልቦናችሁ ተመልሳችሁ የወላጅነት ድርሻችሁን እንድትወጡ እንመክራለን።

እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤት አይለያችሁ!

ብጹዕ : አባ: ዘካርያስ : በኢትዮጵያ : ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን : በሰሜን : ምስራቅና : ምዕራብ አሜሪካ
የኒውዮርክ : ሀገረ : ስብከት : ሊቀ : ጳጳስ :

Abba Zekarias Archbishop of Ethiopian
Orthodox Tewahedo Church Diocese of
New York in Northeast and West U.S.



140-142 W 176th Street Bronx, New York 10453
Tel. 718-466-0600/718-299-2741 Fax 718-466-1271